አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር

6

# አፍሪካ አካዳሚ

# AFRICA ACADEMY

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "የልብ ተግባራት"

3

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

www.AfricaAcademy.com

# መውደድ (አል መሐባ)

- **መውደድ፡-** አላህን፤ ነብዩን፤ ሙእሚን ወንድሞቹን በመውደድ የእምነት ጣዕም ይገኛል፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ሶስት ነገሮች በውስጡ ያሉለት በእነሱ የእምነትን ጣዕም አግኝቷል፡፡ አላህና መልዕክተኛውን ከእነሱ ዉጪ ከሆነ ሁሉ አብልጦ መውደድ፤ ሰውን ሲወድ ለአላህ ብቻ ብሎ መውደድ አላህ ከክህደት ነፃ ካዳረገው በኋላ ወደ ክህደት መመለስን ወደ እሳት እንደመወርወር ያህል መጥላት ነው፡፡›› ብለዋል፡፡
- የውዴታ አትክልት በልቡ የተከለና የዘራ ከዚያም በኢኽላስና ነብዩን መከተል ውሃ ያጠጣህ እንደሆነ የፍሬ አይነቶችን ታፈራለች፡፡ በአላህ ፈቃድም በየጊዜው ፍሬ ትሰጣለች፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- **ማፍቀር አራት አይነት (ክፍል) አለው።**

1) አላህን መውደድህ ነው። እሱም የእምነትህ ዋና መሰረት ነው።

2) ለአላህ ብሎ መውደድ እና ለአላህ ብሎ መጥላት ነው። ይህም ግዴታ ነው።

3) ከአላህ ጋር መውደድ ነው። ይኸውም ከአላህ ጋር ሌላን ማጋራት ነው።

- ይህም አጋሪዎች አምላኮቻቸውን መውደዳቸውን ይመስል ነው። ይህ ክፍል የሺርክ ዋናው ምንጭ ነው።

4) የተፈጥሮ ማፍቀር ነው፡፡ እሱም አባቶች ልጆቻቸውን፤ ልጆች አባቶቻቸውን፤ ባል ሚስቱን፤ ሚስት ባሏን፤ ሰዎች ምግብን መውደድ ይመስል ነው፡፡

- ይህ ክፍል የተፈቀደ ነው፡፡ አላህ እንዲወድህ ዱንያን ችላ በል፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ:-

‹‹ዱንያን ችላ በል አላህ ይወድሓልና›› ብለዋል፡፡